Ethio-Amsterdam Sport and Culture - Postbus 59672, 1040 LD Amsterdam - Tel/Fax: 020 61 80 694 – Web: http://www.ethioamsterdam.com - email: pr@ethioamsterdam.com- k.v.k: 33303362

Date: 19 aug. 10

# መልእክት ከአዘጋጅ ኮሚቴው

ክቡራትና ክቡራን እንግዶቻችን፣

በቅድሚያ እ.ኤ.አ. ካለፈው ጁላይ 29 እስከ 31 - 2010 ዓ.ም. ስምንተኛውን በአውሮፓ የኢትዮጵያውያን ስፖርትና ባህል ፌስቲቫል ለማክበር በአምስተርዳም ከተማ ስለተገኛችሁ ምስጋናችን በያላችሁበት ይድረሳችሁ።

የዘንድሮው የአምስተርዳም ስፖርትና ባህል ፌስቲቫል ከላፉት በዓላት ሁሉ የደመቀና ያማረ፣ በቁጥርም እጅግ የላቀ እንደነበር ተገንዝበናል። የዘንድሮውን ፌስቲቫል በደመቀና ባማረ መልኩ ለማክበር ከልዩ-ልዩ የህብረተሰቡ ክፍሎች የተውጣጣ 8 አባላት ያሉት ኮሚቴ ተዋቅሮ አስፈላጊውን ቅድመ-ዝግጅት ከማድረጉም በላይ እንግዶች ኢትዮጵያዊ ጨዋነት በተሞላው መንገድ በአሉን በሰላምና በደስታ እንዲያሳልፉ የተቻለውን ጥረት አድርጓል።

የአምስተርዳም የበዓል አዘጋጅ ኮሚቴ በዝግጅቱ ልዩ-ልዩ የገቢ ማስገኛ እንቅስቃሴውችም በማድረግ፣ የሚገኘውን ገቢ በሙሉ አንድ የስፖርት ማእከል ለማቋቋም የታቀደ መሆኑን አስቀድሞ አስታውቋል። ከሁሉም በላይ ለእንግዶቻችን ደህንነትና ምቾት ትኩረት በመስጠት ጥራትና ብቃት ያላቸው የመዝናኛ ዝግጅቶችን በአለም እውቅ በሆነው WORLD FASHION CENTRE ማቅረባችን ይታወሳል።

ከተለያዩ ስፍራዎች በሚደርሱን መረጃዎች እንደሚጠቁሙን ከሆነ አብዛኞች እንግዶቻችን በዝግጅቶቻችንና በአጠቃላይ በአምስተርዳም ቆይታዎቻቸው እንደረኩ ገልጸውልናል። ይሁንና በተለይ በቅዳሜው ምሽት በደረሰው ያልተጠበቀ ግርግር አንዳንድ እንግዶቻችን ቅሬታዎቻቸውን ገልጸውልናል። አዘጋጅ ኮሚቴው ቅሬታው ተገቢ መሆኑን በመገንዘብ ከአዘጋጁ ቁጥጥር ውጭ ለተፈጠረው ለዚህ ችግር ከልብ ይቅርታችንን እንገልጻለን።

ጉዳዩን ለማጣራት በደረግነው ሙከራም ይህ ችግር ሊከሰት የቻለው በወቅቱ የነበረው የጥበቃ ክፍል (Security Guards) የአዘጋጅ ኮሚቴውን ፍቃድ ሳይጠይቅ በእንግዶች ላይ ተገቢ ያልሆነ አሰልቺ ፍተሻ በማድረጉ እና ፍተሻው የፈጠረው ረጂም መስመር መሆኑን ተረድተን ጉዳዩንም ለሚመለከተው ክፍል አሳውቀናል። ይኽንን ጉዳይ በቀላሉ የማናልፈው በመሆኑንም ቅርብ ክትትል እያደረግን እንገኛለን።

በምሽቱም ከአንድ ሺህ የማያንሱ ሰዎች ትኬት ሳይቆርጡ የአዳራሹን በር በሃይል በመክፈት ገብተዋል። በወቅቱ የተፈጠረውን ግርግር በመጠቀምም አንዳንድ ስርዓት አልበኞች አስተናጋጆችን በማስፈራራትና ከስፍራው እንዲወገዱ በማድረ የተዘጋጀውን ባር ሙሉ መጠጥ ቀምተዋል። አንዳንዶችም በወርልድ ፋሺን ማዕከል ለትዕይንት የቀረቡ ውድ እቃዎችን ከመስታወት ቡፌ በመስበር መውሰዳቸውን እንዲሁም ሌሎች እዚህ መጥቀስ የማይገባንን ጸያፍ ነገር ማድረጋቸውን የአዳራሹ አስተዳደር ገልጸውልናል። በዚህም ሳቢያ ከ 40 - 70 ሺህ ኤሮ ያህል ኪሳራ ደርሶብናል።

የኢትዮጵያውያን የስፖርትና ባህል ፌዴሬሽን በአውሮፓ

አምስተርዳም ዝግጅት ኮሚቴ